# የተሻሻለው የአፋር ክልል ሕገ መንግስት

# (1994)

# የ1994 ዓመተ ምህረት የተሻሻለው የአፋር ክልል ህገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ

በክልሉ ነዋሪ ሕዝብ ተወካዮች ተመክሮበት የካቲት 8/90 በመጀመሪያ የፀደቀውን እና እስከአሁን ሲሰራበት የቆየውን የክልሉን ህገ መንግሥት በጥልቀት ተመልክቶ በተለይም የክልሉን መንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍልና ተጠያቂነት በግልፅ መደንገግና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት በሚቻልበት ሁኔታ ህገመንግሥቱን ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሥራ ላይ ባለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 99 መሠረት ከዚህ የሚከተለው የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ህገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ________ 1994 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **የተሻሻለው የ1994 ህገ መንግሥት ስለመፅደቁ**

   በአዋጅ ቁጥር 1/1990 ዓመተ ምህረት የፀደቀው የክልሉ ህገ መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ ከታየ በኋላ የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ሕገ መንግሥት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

3. **ስለነባር ሕጎች ተፈፃሚነት**

   በሥራ ላይ ያሉ ማንኛውም ነባር ሕግ ከተሻሻለው ሕገ መንግሥት ጋር ከተቃረነ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

4. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ አዋጅ ከቀን ______ /1994 ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ___ 1994 ዓመተ ምህረት
እስማኤል ዓሊሴሮ
የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ
መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር

## 2. መግቢያ

እኛ የአፋር ሕዝብ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው አፋኝ ስርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን ታፍነው በተዛባ ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ለድህነትና ኋላቀርነት አጋልጦን መቆየቱ፣ በአጠቃላይ ዕድገታችን ያደረሰው አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ በመፈለግ፡፡

የአፋር ሕዝብ ያለፉት የኢትዮጵያ ጨቋኝ ሥርዐቶችን ለመደምሰስ ወደር የሌለው መስዋእትነት ከከፈለበት ምክንያቶች አንዱና ዋናው ሁሉም ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችው የተከበሩ፣ ሕዝቦች በህገ መንግሥትና በሕግ ብቻ የሚተዳደሩ ዲሞክራሲያዊት ሀገር እንድትሆን በማለት በአብዛኛው የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ሕዝቦች ላይ ይፈፀም የነበረው እንግልትና ጭቆና ተጎጂ የሆነ መቆየታችን በማያዳግም ሁኔታ መታረም እንዳለበት በማመን፡፡

መላ የሀገራችን ብሄር፣ ብሄረሰቦች፣ ሕዝቦች ባካሄዱት እልህ ተጋድሎ አድሃሪውና አፋኝ ስርዓት በሚያስተማምን ሁኔታ ተደምስሶ ኢትዮጵያ ሀገራችን የግለሰብ መብቶችና የብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የተከበሩበት እጠቃላይ የህግ የበላይነት የነገሰበት ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሆንዋ የጋራ ዕድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማሕበረሰብ ማነፅ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ፡፡

እኛ የአፋር ሕዝብ ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለዘላቂ ሰላም ለጠንካራ ዲሞክራሲ የምንበቃው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት መሰረት ያደረገና ከብሔራዊ ክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመና የዚህ ክልል ሕዝቦች የተከበሩበትና ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለን የራሳችን ህገ መንግሥት ሲኖረን መሆኑን በሚገባ በማመን፡፡

በሥራ ላይ ያለው ህገ መንግሥት ከክልሉ ነባራዊ የዕድገት ደረጃና የህብረተሰብ አኗኗር ጋር የተጣጣመና ግልፅ አሰራርን የሚከተል በመረጠው ሕዝብ ተጠያቂ የሚሆንና ብቃት ያለው መንግሥታዊ አደረጃጀትን በሚያሳይ አግባብ ቀልጥ መስተካከል ተደርጎበትና የምንገኝበት ሁኔታ በሚጠይቀው መጠን እንደገና ተሻሽሎ መውጣት ያለበት መሆኑን በውል በመረዳት እነሆ ዛሬ ____________ በሠመራ ከተማ ባካሄደነው የክልል ምክር ቤት ጉባኤ ለዚሁ ዓላማ በተሰየመ አካል ተረቅቆ በቀረበው የተሻሻለዉ ህገ መንግሥት ላይ መክረንና በዝርዝር ተወያይተን ስናበቃ በሙሉ ድምፅ አፅድቀነዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ 1
### የክልሉ መንግሥት ሥያሜ

ይህ ህገ መንግሥት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል። በዚሁ መሠረት የተቋቋመው መንግሥት "የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" በሚል ስም ይጠራል።

### አንቀፅ 2
### የአፋር ብሄራዊ ክልል ወሰን

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት መሠረት የቆመ ሆኖ።

በሰሜን ምስራቅ = ኤርትራ

በሰሜን ምዕራብ = ትግራይ ክልል

በደቡብ = ኦሮሚያ ክልል

በደቡብ ምዕራብ = አማራ ክልል

በደቡብ ምስራቅ = ሱማሌ ክልል

በምስራቅ = ጂቡቲ ሪፐብሊክ

የሚያዋስኑት መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ያለው ብሔራዊ ክልል ነው።

### አንቀፅ 3
### ሰንደቅ ዓላማና አርማ

የአፋር ብሔራዊ ክልል የራሱ ሰንደቅ አላማና አርማ ይኖረዋል ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 4
## የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር

የአፋር ብሔራዊ ክልል መዝሙር የሕገ መንግስቱን ዓላማዎች፣ የሕዝቡን የጀግንነት ታሪኩን የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር የዲሞክራሲ ስርዓት አብሮው ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም የክልሉ ሕዝብ ባህል ልዩነትና ብሩህ ተስፋ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 5
## የሥራ ቋንቋ

የክልሉ ብሔራዊ መንግሥት የሥራ ቋንቋ አፋርኛ ነው።

## አንቀፅ 6
## ርዕሰ ከተማ

የክልሉ ርዕስ ከተማ ሠመራ ነው።

## አንቀፅ 7
## የፆታ አገላለፅ

በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ለወንድ ጾታ የተደነገገው የሴቷንም ጾታ ያካትታል።

# ምዕራፍ ሁለት
# የሕገ መንግሥት መሠረታዊ መርሆች

## አንቀፅ 8
## የሕዝብ ወሳኝነት

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ የአፋር ሕዝብ የብሔራዊ ክልሉ መንግሥት የበላይ ስልጣን ባለቤት ነው።
2. የብሔራዊ ክልሉ ሕዝብ የበላይነት የሚገለፀው በሚመርጧቸው ተወካዮችና ራሳቸው በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው።

## አንቀጽ 9
## የሕገ መንግሥቱ የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ

1. ይህ ሕገ መንግሥት የብሔራዊ ክልሉ የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም የባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚነት አይኖረውም።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ይህንን ሕገ መንግሥት የማክበርና የማስከበር እንዲሁም ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።
3. በዚህ ህገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥትን ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

## አንቀጽ 10
## ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።
2. በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

## አንቀጽ 11
## የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

## አንቀፅ 12
## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።
2. ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሣው ይችላል፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
3. ማንኛውም ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል።

# ምዕራፍ 3
# መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

## አንቀፅ 13
## ተፈፃሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካላት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት የመሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌዎች ፌደራላዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችን ሰነዶችና መርሆች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ።

# ክፍል አንድ
# ሰብአዊ መብቶች

## አንቀፅ 14
## የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ የሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው።

## አንቀጽ 15
## በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

## አንቀጽ 16
## የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 17
## የነጻነት መብት

1. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ስርዐት ውጭ ነጻነቱን አያጣም።
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዐት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሠር አይችልም።

## አንቀጽ 18
## ኢ-ሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዐዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በኃይል ተገዶ "ወይም" ግዴታን ለማሟላት የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም።
   ሀ. ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣
   ለ. ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፣

ሐ. የማኅበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ የሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥን ማንኛቸውም አገልግሎት፣

መ. በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈፀምን ማንኛውም የኢኮኖሚና የማህበራዊ የልማት ሥራ።

## አንቀፅ 19
## የተያዙ ሰዎች መብት

1. ወንጀል ፈፅመዋል በማባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው።
2. የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት ያላቸው ስለመሆኑና ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው።
3. የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው። ይህም ጊዜ ሰዎች ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለዉ ጉዞ የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡም በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለፅላቸው መብት አላቸው።
4. የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደብ መሠረት ፍርድ ቤት በመቅረብ የተያዙበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዙት ሰዎች በጥበቃ ስር እንዲቆዩ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዙት ሰዎች በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ያላቸውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት።
5. የተያዙት ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማንኛውም ማስረጃ እንዲያመጡ አይገደዱም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።
6. የተያዙት ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው። ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች መሠረት ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

## አንቀጽ 20
## የተከሰሱ ሰዎች መብት

1. የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሕዝባዊ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው። ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት የሕዝብን የሞራል ሁኔታና የአገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸውና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት አላቸው።
3. ማንኛውም ተከሳሽ በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለቸው።
4. የተከሰሱት ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት ወይም ምስክሮች ተቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው። እንዲሁም ለመከላከል የሚያስችላቸው ማንኛውም ማስረጃ የማቅረብ ወይም እንዲቀርብላቸው የማድረግና ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።
5. የተከሰሱ ሰዎች በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ የማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው።
6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው።
7. የፍርዱ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።

## አንቀጽ 21
## በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1. በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው።
2. ከትዳር ጓደኞቻቸውና ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከሀይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸውና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኙአቸው ዕድል የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀፅ 22
## የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበትን ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመ ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛው ሰው ላይ አይወሰንም።
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 1 ድንጋጌ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሽ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## አንቀፅ 23
## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግና ሥነሥርዐት ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

## አንቀፅ 24
## የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብአዊ ፍጡርነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው ሰብዐዊ ክብሩንና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው።
3. ማንኛውም ሰው የራሱን ሰብእናና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው።

## አንቀፅ 25
## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸው ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀፅ 26
## የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል።
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።
3. የመንግሥት ባለስልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብ ሰላምን፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነቶች በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሠረቱ ዝርዝር ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም።

## አንቀፅ 27
## የሃይማኖት፣ የህሊናና የእምነት ነፃነት

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና የሀይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት መያዝ ወይም የመቀበል ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ የመከተል የመተግበር የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል።
2. በፌደራል ሕገ መንግሥት አንቀፅ 90 ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስፈልጓቸውን የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ።
3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በሃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።
4. ወላጆችና ሌሎች ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ስነምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው።
5. ሃይማኖትንና እምነትን የመግለፅ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ የሌሎች ዜጎች መሰረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል።

## አንቀፅ 28
## በሰብዕና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የሀገሪቱ ሕጎች ፣ በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች በተለይ የሰው ዘር ማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምህረት በይቅርታ አይታለፍም።

# ክፍል ሁለት
## ዲሞክራሲያዊ መብቶች

## አንቀፅ 29
## የአመለካከት፣ ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።

2. ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለፅ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት፣ በስነጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውም አይነት መረጃና ሀሳብን የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።

3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል።
   ሀ. የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑ፣
   ለ. የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት መሆኑ፣

4. ለዲሞክራሲያዊ ስርዐት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል።

5. በከፊሉ ወይም በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄደው ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።

6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው ◦ የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም። በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዐዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናሉ።

7. ማንኛውም ሰው ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦች ጥሶ ከተገኘ በህግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

## አንቀፅ 30
## የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጪ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይነካ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ስርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።
2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ህጎች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

## አንቀፅ 31
## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት መንገድ የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።

## አንቀፅ 32
## የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሀጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወርና መኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ ሰርቶ የመኖር፣ ሀብት ንብረት የማፍራት፣ የመሸጥ፣ የማስተላለፍ፣ የማውረስ እና የመያዝ እንዲሁም በፈለገ ጊዜ ከክልሉ የመውጣት መብት አለው።

## አንቀፅ 33
## የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር በብሔር ብሔረሰብ በሃይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍችም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ።
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሰረታል።
3. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው ከሕብረተሰቡና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።
4. በህግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርአቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል።
5. ይህ ሕገ መንግሥት የግል የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖታዊ በባህላዊ ሥርዐት መሠረት መዳኘትን አይከለክልም ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 34
## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ሕገ መንግሥት በአረጋገጠላቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።
2. ሴቶች በዚህ ሕገመንግሥት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ጠባሳ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በግል ተቋማት ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳድረው ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡

4. ሴቶች ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግሥት ማስከበር አለበት፡፡ ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፡፡

5. ሴቶች የቅጥር፣ የስራ ዕድገት፣ እኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፡፡

   ሀ. የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፡፡ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት ፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል፡፡

   ለ. የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሠረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል፡፡

6. ሴቶች በእርግዝና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው፡፡

7. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች እኩል መብት አላቸው፡፡ እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡

8. ሴቶች በብሔራዊ ክልሉ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

## አንቀፅ 35
## የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፡፡

   ሀ. በህይወት የመኖር፣

   ለ. ስምና ዜግነት የማግኘት፣

   ሐ. ወላጆችን ወይም በህግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

መ. ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፤

ሠ. በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፡፡

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች፣ ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።

3. ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግሥት ወይም የግል እጓለማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው፡፡

4. ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው።

5. መንግስት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻችና የሚያበረታታ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል።

## አንቀፅ 36
## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከተው ውሳኔ ወይም ፍርድ፣

ሀ. ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል

ለ. ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

## አንቀፅ 37

## የአፋር ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት

የአፋር ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው። በዚህ መሠረት የአፋር ሕዝብ፦

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ የማሳደግ፣ ባህሉን የመግለፅ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለው።
2. በራስ መልክዓ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመወሰን፣ በራስ የማስተዳደርና እንዲሁም በፌደራላዊ መንግስት ውስጥ በእኩልነት፣ ተገቢና ፍትሀዊ የሆነ የውክልና አግባብ ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ መብት አለው።
3. የአፋር ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር መብት፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል መንግስት አስተዳደር ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እስከ ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሱት መብቶች ታግዶ፣ ተረግጦ፣ ወይም ተሸራርፎ ብሎ ባመነበትና ባጋጠሙት ስር ሆኖ ሊያስተካክላቸው ባልቻለበት ጊዜ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 39 በተደነገገው መሠረት የራሱን ዕድል በራሱ እስከ መገንጠል ድረስ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል።
5. የአፋር ሕዝብ የራሱን ዕድል የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያለ መብት በሥራ ላይ የሚውለው፦
   ሀ. የመገንጠል ጥያቄ በሕግ አውጭ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ የድምፅ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ
   ለ. የፌደራሉ መንግሥት የሕዝብ ምክር ቤቱ የመገንጠል ውሳኔ በደረሰው በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሕዝብ ውሳኔ እንዲያካሂድ ሲያረጋግጥ፣
   ሐ. የመገንጠል ጥያቄ በሕዝብ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ፣
   መ. የፌደራሉ መንግሥት መገንጠሉ ለመረጠው የአፋር ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ
   ሠ. በሕግ በሚወሰነው መሠረት በፌደራል መንግሥትና በመገንጠል የወሰነው የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት መካከል የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።
6. በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ " የአፋር ሕዝብ" ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያሉት፣ የአፋርኛ ቋንቋ የሚናገር፣ የጋራ ወይም የተያያዘ ህልውና አለኝ ብሎ የሚያምንና በአብዛኛው በተያያዘ መልክአምድር የሚኖር ሕብረተሰብ ነው።

## አንቀፅ 38
## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆን ይከበርለታል፡፡ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም፣ ወይንም የሌሎችን ዜጎች መብቶችን እስካልተቃረኑ ድረስ ንብረት የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም ለሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶች ያካትታል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ዓላማ "የግል ንብረት" ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው አገር አቀፍ ወይም ክልላዊ ማሕበራት፣ ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤቶች፣ እንዲሆኑ በተፈቀደላቸው ማሕበረሰቦች በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው፡፡
3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ ሕዝብ የጋራ ንብረት ነው፡፡
4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡
5. በክልሉ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት ያስከብርላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡
6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ የሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል፡፡ ዝርዝሩም በሕግ ይወሰናል፡፡
7. ማንኛውም ሰው በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል ዝርዝር አፈፃፀሙ በሕግ ይወሰናል፡፡
8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 39

## የኢኮኖሚያዊ፣ የማሕበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪና በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን ሥራውንና መኖሪያውን የመምረጥ መብት አለው።
3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄደው ማህበራዊ አገልግሎት በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።
4. የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።
5. የክልሉ መንግስት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።
6. የክልሉ መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል እንዲሁም በሚካሄደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።
7. የክልሉ መንግሥስት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።
8. አርብቶ አደሮችና ገበሬዎች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውንና ለብሔራዊ ሃብት ካደረጉት የምርት አስተዋፅኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት።
9. የክልሉ መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ስነ ጥበብና ስፖርት መስፋፋት አስተዋፅኦ የማድረግ ሃላፊነት አለበት።
10. የክልሉ አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች የብድር አገልግሎት እንዲሁም ስለእንስሳት እርባታና ግብአቶች ያመች ዘንድ መንገድ፣ ገበያና ሌሎች መሠረተ ልማቶች እንዲዘረጉ ልዩ ጥረት ያደርጋል።

## አንቀጽ 40
## የሠራተኛ መብት

1. የፋብሪካና የአስተዳደር ሠራተኞች የእርሻ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች
   ሀ. የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው፤ ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትንና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት ከአሰሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል።
   ለ. በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ የማቆምን ጨምሮ ቅሬታ የማሰማት መብት አላቸው።
   ሐ. በንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) መሠረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ።
   መ. ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።
2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት፣ የመዝናኛ ጊዜ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።
3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዐት ይደነግጋል።

## አንቀጽ 41
## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታዎችን የማሻሻልና የማያቋርጥ ዕድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።
2. የክልሉ ነዋሪዎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ በሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።
3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች ዕድገትን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ይሆናል።

## አንቀፅ 42
## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።
2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ ዕርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዛወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው።

# ምዕራፍ አራት
# የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የስልጣን ክፍፍል

## አንቀፅ 43
## የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. ክልሉ በቀበሌ፣ በወረዳ ወይም በከተማ እንዲሁም በክልል ምክር ቤት የተዋቀረ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ ም/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖች ሊያዋቅርና ስልጣንና ተግባራቸውን ሊወስን ይችላል።
2. የክልሉ ነዋሪ የሆነው የአርጎባ ህዝብ የልዩ ወረዳ ውክልና በዚህ ህገ መንግስት ተረጋግጧል።

## አንቀፅ 44
## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ መንግሥት ህግ አውጪ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለመረጠው ህዝብ ነው።
2. የክልሉ ከፍተኛ የህግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

## አንቀፅ 45
## የክልሉ መንግስት ስልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ውስጥ በግልጽ ተለይተው ለፌደራሉ መንግሥት ወይም ለፌደራሉ መንግስትና ለክልሉ መንግስት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጭ ያሉ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግስት ተግባር ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊ መንግስቱ
   ሀ. የክልሉን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ ዕቅድ ያወጣል ያስፈጽማል።
   ለ. የክልሉን ህገ መንግሥትና ሌሎች ህጎችን ያወጣል ያስፈጽማል።
   ሐ. የፌደራሉ መንግሥት በሚያወጣው ህግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሃብትን ያስተዳድራል፣
   መ. ራስን በራስ ማስተዳደር ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል የህዝ የበላይነት የሠፈነበትን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት ይህንን ህገ መንግስት ይጠብቃል፣ ይከታተላል።
   ሠ. በክልሉ ውስጥ መሠረታዊ የኢንቨስትመንት ሀብት ልማትና ግብርና ልማት በአጠቃላይ በተብርና ልማት ሰራዎች ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ሰራዎቹ በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
   ረ. የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት የስልጣንና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።
   ሰ. የክልሉን ፖሊስ ኃይል ያደራጃል ይመራል የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል።
   ሸ. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 28ንዑስ አንቀጽ 1 እና የዚህ ህገመንግሥት አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በህግ መሠረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል።
   ቀ. ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶች ይጥላል ይሰበስባል የክልሉን በጀት ያዘጋጃል ያፀድቃል ያስተዳድራል።
   በ. በክልል መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የስራ ግብር ይጥላል ይሰበስባል።
   ተ. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያን ይወስናል ይሰበስባል።
   ቸ. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል ይሰበስባል።

ነ. በክልሉ በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል ይሰበስባል በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል።

ኘ. በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሠረት ይሰበስባል።

ኀ. ከፌደራል መንግስት ጋር

1. ጋራ ከሚያቋቁማቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር የሥራ ግብር የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሠረት ይካፈላል።
2. ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ላይና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በህጉ መሠረት ይካፈላል።
3. ከከፍተኛ የማዕድን ስራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በህጉ መሠረት ይካፈላል።

አ. በክልል መስተዳድሩ አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል።

ከ. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል።

ወ. በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በስራ ላይ ያውላል።

## ምዕራፍ አምስት
## ስለ ክልሉ ም/ቤት

### አንቀጽ 46
### ስለክልሉ ምክር ቤት አባላት

1. የክልሉ ምክር ቤት አባላት ነፃ ቀጥተኛ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በህዝብ ይመረጣሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
3. የምክር ቤቱ አባላት የመላው የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ናቸው። ተገዥነታቸውም

   ሀ. ለህገ መንግሥቱ፣

   ለ. ለመረጣቸው ህዝብና

   ሐ. ለህሊናቸው ብቻ ይሆናል።

4. ማንኛውም የምክር ቤት አባል በምክር ቤት ውስጥ በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰድበትም።

5. ማንኛውም የክልል ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም በወንጀል አይከሰስም።

6. ማንኛውም የምክር ቤት አባል የመረጠው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በህግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነት ይወገዳል።

## አንቀፅ 47
## የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ምክር ቤት በዚህ ህገ መንግስት መሠረት የክልሉ ህግ አውጪ አካል ነው።
2. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በብሔራዊ ክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ስር የሰፈረው አጠቃላይ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በተለይ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

   ሀ. በዚህ ህገመንግሥት መሠረት የፌደራሉን ህገመንግስትና ሌሎች ህጎችን የማይጻረሩ ልዩ ልዩ ህጎች ያወጣል።

   ለ. የህዝቡን ብዛት የክልሉን ስፋትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አመን ውስጥ በማስገባት በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነው።

   ሐ. የፌደራሉ መንግስት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጎራባች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ጋር የሚደረጉ ስምምነቶችን ያፀድቃል።

   መ. የራሱን አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ ይመርጣል። ለምክር ቤቱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያሰይማል።

   ሠ. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድሩን በምርጫ ያሰይማል፤ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ምክትል መስተዳድርና የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል።

   ረ. በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ዋና ኦዲተሩንና ምክትል ዋና ኦዲተሩን ይሾማል።

   ሰ. የክልሉ፣ የዞንና የወረዳ የዳኝነት አካላትን ያቋቁማል።

   ሸ. የኦዲትና የቁጥጥር አካሉን ያቋቁማል።

   ቀ. በህጉ መሠረት ምህረት ያደርጋል።

   በ. የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ያወጣል የፀጥታና የፖሊስ ሃይሉን ያቋቁማል።

   ተ. የብሔራዊ ክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች ያፀድቃል።

ቸ. የብሔራዊ ክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ህጎች ያወጣል የክልሉን በጀት መርምሮ ያፀድቃል።

ነ. ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠንና ለዲሞክራሲያዊ ስልጣን ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል።

ኘ. ለክልሉ መንግስት በተከለለው የገቢ ምንጭ በክልሉ ውስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል።

አ. የክልሉ መስተዳድሩን የሠራተኛ አስተዳደር የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል።

ከ. በዚህ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 2 (ዐ) ሥር ለክልሉ መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል።

ወ. በተለይ በግብርና ልማት ስር የእንስሳት ሀብት ልማት እና የገጠር ልማት ወዘተ የስራ እንቅስቃሴዎች በመስተዳድር ምክር ቤቱ እና በቀጥታ ጉዳዩ በሚመለከተው አስፈፃሚ አካል እየተከናወኑ መሆናቸውን ይከታተላል።

ኀ. የሀገሪቱንና የክልሉን ህገ መንግስታት፣ አዋጆችና ሌሎች ህጎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር የማስፈጸሚያ ደንቦችን ያወጣል።

ዐ. የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግስት ባለስልጣናት ለጥያቄ ይጠራል። የአስፈጻሚውን አካል አሠራር ይመረምራል።

## አንቀፅ 48
## ስለ ክልሉ ምክር ቤት

1. የክልሉ ምክር ቤት የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የጽህፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 49
## ስለ ምክር ቤቱ አፈጉባኤ አሰያየምና የስራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት አፈጉባኤ በዚህ ህገመንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሠ) መሠረት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
2. የአፈ ጉባኤው የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀፅ 50
## <u>የአፈ-ጉባኤ ስልጣንና ተግባር</u>

የክልሉ ምክር ቤት አፈ. ጉባኤ በዚህ ህገመንግስት መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል ይመራል።
2. ምክር ቤቱን በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል።
3. የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል።
4. ምክር ቤቱ በአባሎች ላይ እንዲጠበቁ የወሰነው የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል።
5. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀፅ 51
## <u>የምክትል አፈ-ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል አፈ-ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባኤውና ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ፡

1. በአፈ-ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

## አንቀፅ 52
## <u>የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን</u>

1. የክልሉ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከሁለት ሶስተኛው በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ የስብሰባው ምልአተ-ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል።
3. የክልሉ ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት ለአምስት ዓመታት ነው የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።
4. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛው በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ በጠየቁ ጊዜ አፈ-ጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

5. የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል። ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ወይም በክልሉ አስፈጻሚ አካል በተጠየቀና በምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉት ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

## አንቀፅ 53
## የምክር ቤቱ ውሳኔዎችና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓቶች

1. በዚህ ህገ መንግስት ውስጥ ተገልጾ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይሆናል።
2. ምክር ቤቱ ውስጣዊ አሠራሩንና የህግ አወጣጡን ሂደት አስመልክቶ ዝርዝር ደንቦችን ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል።

# ምዕራፍ ስድስት
# የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የህግ አስፈፃሚ አካል መቋቋም

## አንቀፅ 54
## የአስፈፃሚነት ሥልጣን

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤት ነው።
2. ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ ለሚፈፅሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀፅ 55
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀር

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የአስፈፃሚ ቢሮዎች ኃላፊዎችና በህግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው።
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ ነው።
3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩነው።
4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወስነው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል።

## አንቀፅ 56
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የፌደራሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በክልሉ ምክር ቤትና በፌደራሉ መንግስት የወጡ ህጎችና የተላለፉ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በስራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል።
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስፈፃሚ አካላትና የሌሎች ተቋማት አደረጃጀት ይወስናል። ስራቸውን ይከታተላል በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።
3. የክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይነድፋል፤ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል የተወሰነውንም ያስፈፅማል።
4. በክልሉ ውስጥ ህግና ስርዐት መከበሩን ያረጋግጣል በህግ መሠረት ይቅርታ ያደርጋል።
5. የክልሉ ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል።
6. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ረቂቅ አዘጋጅቶ ለክልል ምክር ቤት ያቀርባል።
7. በዚህ ህገ መንግሥት አንቀፅ 47 ንዑስ አንቀፅ 2 (ወ) ሥር ለክልል ምክር ቤት አስቀድሞ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በስራ ላይ ያውላል።
8. የክልሉ የአርብቶ አደር የኑሮ ሁኔታ የተሻለና ከዐላ ቀር አሠራር የሚላቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል።
9. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀፅ 57
## የከተማ ምክር ቤትን ስለማቋቋም

የክልል ም/ቤት የከተሞችን የእድገት ደረጃና ልዩነትን ባገናዘበ መልኩ የከተማ ም/ቤቶችን ያቋቁማል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 58
## የርዕሰ መስተዳድሩ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. ርዕሰ መስተዳድር በክልሉ ምክር ቤት ውስጥ በአብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከክልሉ ምክርቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል።
2. በዚህ ህገ መንግስት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕሰ መስተዳድሩ የስራ ዘመን የብሔራዊ ክልል ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው።

## አንቀፅ 59
## የርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ መስተዳድር ስራ መሪ፣ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና የብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ነው
2. ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ፦
   ሀ. የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል ያስተባብራል ይወክላል።
   ለ. የክልሉ መንግስት ህግ አውጪና ህግ አስፈፃሚ አካላት በየበኩላቸው መክረው ያፀደቋቸውን አዋጆችና ደንቦች "በአፋር ነጋሪት ጋዜጣ" ይታወጁ ዘንድ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ፈርሞ ይልካል።
   ሐ. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል።
   መ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር መርጦ ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስሾማል።
   ሠ. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን የዞን አስተዳዳሪዎችንና የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችን ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል።
   ረ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ፊደል ተራ ቁጥር 'መ' እና 'ሠ' ሥር የሠፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁኔታ ከምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፣ከዞን አስተዳዳሪዎች በመለስ ያሉትንና ከላይ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል።
   ሰ. ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ውጭ የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎች ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች፣ ኮሚሽነሮች መምሪያ ኃላፊዎችና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች መርጦ ይሾማል።
   ሸ. የብሔራዊ ክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።
   ቀ. በክልሉ የሚገኙትን የበታች የአስተዳደር እርከኖች ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል ይቆጣጠራል።
   በ. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።
   ተ. ዝርዝሩ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ሆኖ አስፈላጊነታቸው እየታየ በተመረጡ ስፍራዎች የክልል መስተዳድሩን የሚወክሉና

ለወረዳዎች ሁለተናዊ ድጋፍ የሚሰጡ የአስተዳደር አካባቢ ተጠሪ ጽሕፈት ቤቶች ያቋቁማል። አስተዳዳሪዎችንና ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ይሰይማል።

## አንቀፅ 60
## የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ከብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት መካከል በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ. በርዕሰ መስተዳድሩና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
   ለ. ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።
2. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው።

## አንቀፅ 61
## የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በህገ መንግስቱ የተሰጠውን ሥልጣን ለመወጣት ያስችለው ዘንድ የራሱ የሆነ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈትቤት የመስተዳድሩ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል።
3. የጽሕፈት ቤቱ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 62
## ስለ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

1. የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የእለት ተእለት ሥራዎች የሚያከናውኑ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎች ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ተቋማት እንዳስፈላጊነታቸው ይቋቋማሉ።
2. የቢሮዎችና ሌሎች ከፍተኛ ተቋማት ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለመስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ያልሆኑ ቢሮዎችና ሌሎች ተቋማት ተጠሪነት ከተቋቋሙበት አላማና

ከሚያስፈልጉት ተልዕኮ ጋር አግባብነት ባላቸው የክልሉ መንግስት የበላይ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ይሆናል፣ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 63
## የሽማግሌዎች ጉባኤ ስለማቋቋም

የክልሉ ምክር ቤት እንደ አስፈላጊነቱ የአገር ሽማግሌዎች ጉባኤ በተለያየ እርከን ያቋቁማል ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

# ምዕራፍ ሰባት
# ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

## አንቀፅ 64
## ስለነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. የክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ መንግስት ተቋቁሟል
2. የዳኝነትን ሥልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በህግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጪ የሚያደርግና በህግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።

## አንቀፅ 65
## ስለባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ የዳኝነት አካል

በዚህ ሕገ መንግስት አንቀፅ 64 ንዑስ አንቀፅ 2 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ህገ መንግስት ከመፅደቁ በፊት በመንግስት ዕውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካል በዚህ ህገመንግስት ዕውቅና አግኝተው ይደራጃሉ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 66
## የዳኝነት ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው።
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል፣ ከማናቸውም የመንግስት አካል ባለስልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው።

3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ። ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።
4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በህግ የተወሰነው የጡረታ እድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ስራው አይነሳም።
   ሀ. የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲፕሊን ህግ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ግልፅ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም
   ለ. በህመም ምክንያት የዳኝነት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና
   ሐ. የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ የአብላጫ ድምፅ ሲደገፍና ሲፀድቅ
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት አንድ ዳኛ ከዳኝነት ሥራው የሚያስነሳው ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ጉባኤው ከወሰነበት ጉዳዩ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ እስኪታይ ድረስ ከዳኝነት ስራው ታግዶ መቆየት ይኖርበታል።
6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

## አንቀፅ 67
## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በወረዳ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል። የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት
   ሀ. ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ስልጣን፣
   ለ. በፌደራል ጉዳዮች ላይ የፌደራሉ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን፣
   ሐ. ማናቸውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካለው ክልላዊ ስልጣን በተጨማሪ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሆን ይዳኛል።
4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል።

5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌደራል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል።
6. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።
7. የክልሉ ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚፈፅሙትን ፌደራላዊ የዳኝነት ተግባር ለማከናወን የሚያወጡትን ገንዘብ ወጪ በተመለከተ ከፌደራል መንግስት ማካካሻ እንዲሰጣቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል።

## አንቀፅ 68
## ስለ ዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች እና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።
3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌደራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በእጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልል ምክር ቤት የማቅረብ ሃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌደራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀውን አስተያየት በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የእጩ ዳኞችን ሹመት ያፀድቃል።

## አንቀፅ 69
## ስለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል።
2. የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ጉባኤውን በሊቀመንበርነት ይመራል።
3. የጉባኤው አባላት ዝርዝር ስብጥር ስልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 70
## ሕገ መንግስቱን ስለመተርጎም

1. በክልሉ ውስጥ የሕገ መንግስታዊ ክርክር ጉዳይ ወይም የትርጉም ጥያቄ ሲነሳ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የወረዳ ምክር ቤቶች የተውጣጡ አንዳንድ አባላት ተውጣጥተው የሚሰየም የሕገ መንግስት ተረጓሚ ኮሚሽን በዚህ ሕገመንግሥት ተቋቁሟል።
2. ኮሚሽኑ የክልሉ ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች ላይ መክሮ በስልሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋመው ኮሚሽኑን አገልግሎት ዘመን አምስት ዓመት ሲሆን ሕገመንግስታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ይሰበሰባል።
4. ኮሚሽኑ የራሱን ሰብሳቢና ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል መርጦ ሥራውን የሚያከናውን ሲሆን ለሥራው የሚያስፈልገው የጽህፈት ቤት አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ከክልሉ ምክር ቤት ያገኛል።

## አንቀፅ 71
## የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል።
2. የክልሉ ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አስራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።
   ሀ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት - - - - ሰብሳቢ
   ለ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት - - - - ምክትል ሰብሳቢ
   ሐ. በክልል መስተዳድር ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በብሔራዊ ክልል ምክር ቤት የሚሾሙና በሙያ ብቃታቸውና በስነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች - - - - አባላት
   መ. በአፈጉባኤው አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየሙ 3 ተወካዮች - - - - አባላት

## አንቀፅ 72
## የአጣሪ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ይህንን ሕገመንግሥት መሠረት አድርገው ከብሔራዊ ክልሉ የሚመነጩ ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች የማጣራት ስልጣን ይኖረዋል። በሚያደርገው ማጣራት መሠረትም የክልሉን ሕገ መንግስት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ

ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የራሱን የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል።

2. አጣሪ ጉባኤው በክልሉ መንግስት አካላት የሚወጡ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማናቸውም ሁኔታ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሊቀርብለት ከመረመረና ካጣራ በኋላ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኮሚሲዮኑ ያቀርባል።

3. በፍርድ ቤቶች በኩል የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ አጣሪ ጉባኤው

   ሀ. የክልሉን ህገመንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል። ሆኖም ባጣሪ ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታውን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለኮሚሲዮኑ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

   ለ. የህገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ ሚሰጠውን ህገመንግስታዊ ትርጉም አሰናድቶ ለኮሚሽኑ ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል።

# ምዕራፍ ስምንት
## ስለ ወረዳ መስተዳድር አደረጃጀት እና ስልጣን

### አንቀፅ 73
### አደረጃጀት እና አሰራር

የወረዳ መስተዳድር ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በታች የሚደራጅ የመንግስት አስተዳደር መዋቅር ሆኖ የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል።

1. በስሩ ከተደራጁ ቀበሌዎች በሚወከሉ የሕዝብ ተመራጮች ተዋቅሮ የሚቋቋም የወረዳ ምክር ቤት
2. ከዚሁ ምክር ቤት አባላት መካከል ተመርጦ በሚሰየም የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አማካኝነት የሚቋቋም የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት
3. በዚህ ሕገ መንግስት መሠረት የተቋቋመ የወረዳ የዳኝነት አካል

### አንቀፅ 74
### የወረዳ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ መስተዳድር በተደራጀበት አካባቢ የኢኮኖሚያዊ ልማት እና ማሕበራዊ አገልግሎት እቅዶችን ለማዘጋጀትና ለመወሰን ሆኖ የክልሉ መንግስት አካላት

በየጊዜው የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ስልጣን ይኖረዋል።

2. እያንዳንዱ ወረዳ እራሱን የሚያስተዳድር፣ አካባቢውን የሚያለማትና በውስጣዊ ጉዳዩ ላይ ሙሉ የመወሰን መብት እና ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ምክር ቤት ተጠሪ የሚገኝ የበታች አካል ነው።

## አንቀፅ 75
## ስለወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥ እና ተጠሪነት

1. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳው የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ።
2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ይሆናል።

## አንቀፅ 76
## የወረዳ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ ከፍተኛው መንግስታዊ የስልጣን አካል ነው። ተጠሪነቱም ለክልል ምክር ቤት ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ሥር የሠፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ. የወረዳውን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ አስተዳደራዊ የስራ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞች ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል።
   ለ. በወረዳው ውስጥ መሠረታዊው የእንስሳት ሀብት ልማት እና የግጦሽ ልማት በአጠቃላይ የግብርና ልማት ስራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መከናወኑን ይከታተላል።
   ሐ. ነዋሪውን ሕዝብ ለልማት ስራ በስፋት የሚያንቀሳቅሱበትንና የሚንቀሳቀሱበትን አመች ሁኔታ ይፈጥራል።
   መ. ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ ከምክር ቤት አባላት መካከል አፈጉባኤውን ምክትል አፈ ጉባኤውንና ዋና አስተዳደሪውን በምርጫ ይመድባል። ዋና አስተዳዳሪው የሚያቀርባቸውን የወረዳ ምክትል አስተዳደሪ እና የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ተቀብሎ ያፀድቃል።
   ሠ. የራሱን ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ስርዓት መጠበቂያ መመሪያ ያወጣል።

ረ. ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ የመሬት መጠቀሚያ ታክስን የእርሻ ስራ ገቢ ግብርንና ሌሎች ገቢዎች መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል ሌሎች የአገልግሎት ታክሶችን እና ክፍያዎችን ይጠቀማል።

ሰ. የራሱን በጀት መርምሮ ያፀድቃል ከክልሉ ከሚመደበውና ከሚያስተዳድረው ውጭ ያለውንና የወረዳውን የገቢ ምንጭ ይጠቀማል።

ሸ. የፌዴራሉ እና የክልሉ ሕገ መንግስታትና ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳውን ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ አውጥቶ በስራ ላይ ያውላል።

ቀ. የወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች የወረዳውን ባለስልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፡ የአስፈፃሚውን አካል አሠራር ይመረምራል።

## አንቀፅ 77
## ስለምክር ቤቱ አመራር

1. የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት እንዲኖረው ሆኖ ከአባላቱ መካከል ተመርጠው በሚሰየሙ አንድ አፈ ጉባኤና አንድ ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 78
## ስለ ወረዳ አፈ ጉባኤ ስልጣን

አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ

1. ወቅቱን ጠብቆ ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራትና ጉባኤውን የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል።
2. ሌሎች የአፈ ጉባኤው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች የክልል ምክር ቤቱን አፈ ጉባኤ አስመልክቶ በዚህ ሕገመንግስት የተደነገጉት እንደየአግባቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀፅ 79
## ስለ ወረዳ ምክትል አፈ ጉባኤ ስልጣን

ምክትል አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤውና ለወረዳ ምክር ቤት ሆኖ

1. በአፈ ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡
2. አፈ ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

## አንቀፅ 80
## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜ እና የስራ ዘመን

1. የወረዳ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከሁለት ሶስተኛው (2/3) መካከል በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤ የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።
3. የወረዳ ምክር ቤት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል የቀድሞው ምክር ቤት የስራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ ምክር ቤት ስራውን ይጀምራል።
4. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው የምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀፅ 81
## ስለ ወረዳ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት

የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል። ሆኖም ምክር ቤቱ የራሱን ጽሕፈት ቤት እስኪያደራጅ ድረስ የመስተዳድር ምክር ቤቱንና የዋና አስተዳዳሪውን ጽሕፈት ቤት እና የቢሮ መገልገያዎች በመጋራት ይሠራል።

## አንቀፅ 82
## ስለ ወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት

1. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ ሕግ አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለዋና አስተዳዳሪውና ለወረዳው ምክር ቤት ነው።
2. የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት የወረዳው አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም በወረዳው ውስጥ የተቋቋሙ ዋና ዋና አስፈፃሚ የሴክተር ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች የሚገኙበት አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪው ይሆናል።

## አንቀፅ 83
## ስለወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡
   ሀ. የፌዴራሉና የክልሉ መንግስታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶች እና ፕሮግራሞች በተቋቋመበት ወረዳ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡
   ለ. በወረዳው ውስጥ ያሉ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ያስተባብራል ሥራቸውን ይከታተላል ይመራል፡፡
   ሐ. የወረዳውን አመታዊ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ለምክር ቤቱ ያቀርባል ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
   መ. የወረዳውን ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣ የወረዳውን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል ሥራቸውን ያስተባብራል፡፡
   ሠ. የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
   ረ. የተፈጥሮ ሃብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል ሕዝቡን ለልማት ስራ በስፋት ያነሣሣል፡፡
   ሰ. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም ቅርፃ ቅርጽ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል፡፡
   ሸ. በወረዳው ያሉ አርብቶ አደሮችን የኑሮ እንቅስቃሴን ይከታተላል በእንስሳት ሀብት በግጦሽ ልማት እና በመጠጥ ውሃ ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል ይቆጣጠራል፡፡
   ቀ. በሕግ መሠረት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ስራ ገቢ ግብር እና ሌሎች ግብሮችን ይሰበስባል ተጨማሪ ግብሮች ስለሚገኙበት ሁኔታ አጥንቶ ለወረዳው ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፡፡
   በ. በወረዳው ምክር ቤት እና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
2. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግስታዊ ስልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባር እና ለሚያሳልፉት ውሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 84
## ስለ ወረዳው አስተዳደሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ከወረዳው ምክር ቤት አባላት መካከል አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት አቅራቢነት በወረዳው ምክር ቤት ይሰየማል፡፡
2. በዚህ ሕገ መንግስት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳው አስተዳዳሪ የስራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 85
## የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነት ለወረዳው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሆኖ የተቋቋመው የወረዳ መስተዳድር ተጠሪና የአስተዳደሩ ስራ መሪ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው፦
   ሀ. የወረዳውን አስተዳዳሪ ይወክላል ።
   ለ. የወረዳውን መስተዳድር ምክር ቤት ይሰበስባል፣ ይመራል።
   ሐ. የፌዴራሉንና የክልሉ መንግስታት ፖሊሲዎች ሕጎች፣ ደንቦች መመሪያዎችና፣ ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።
   መ. ምክትል አስተዳዳሪውን ጨምሮ የወረዳውን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለወረዳው ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል።
   ሠ. የወረዳው አስተዳደሩን ልዩ ልዩ ተቋማትንና በስሩ የሚገኙትን ተቋሞች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል ይመራል ይቆጣጠራል።
   ረ. የወረዳው ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና እቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።
   ሰ. የወረዳው ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ሕግና ስርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።
   ሸ. ለወረዳው ምክር ቤት ለወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት እና ለበላይ የመስተዳድር አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል።
   ቀ. በወረዳው ምክር ቤት እና በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀፅ 86
## የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ

1. የወረዳ አስተዳዳሪው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።
2. በወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀፅ 87
## የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ጽሕፈት ቤት

1. የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የዋና አስተዳዳሪው ጽሕፈት ቤት የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ሊያገለግል ይችላል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

# ምዕራፍ ዘጠኝ
## ስለ ቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀፅ 88
### አደረጃጀት እና ተጠሪነት

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻው መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ሲሆን በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ለታቀፈበት የወረዳ ወይም ከተማ መስተዳደር ይሆናል።
2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል፡-
   ሀ. የቀበሌ ምክር ቤት
   ለ. የመስተዳድር ምክር ቤት
   ሐ. የማህበራዊ ፍርድ ቤት

### አንቀፅ 89
### ስለ ቀበሌ ምክር ቤት

1. የቀበሌ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ ተቋቁሟል።
2. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ።
3. የምክር ቤቱ አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ነው።
4. የቀበሌው ምክር ቤት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት የከተማ ምክር ቤት ወይም የወረዳ ምክር ቤት ይሆናል።

### አንቀፅ 90
### የቀበሌ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የወረዳው ምክር ቤት እና የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት በየጊዜው የሚያወጧቸውን መመሪያዎች እና ዕቅዶች በቀበሌው ውስጥ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

2. የበላዩ የሆኑት የአስተዳደር አካላት ከሚያወጧቸው ፖሊሲዎች ሕጎች ደንቦች እና መመሪያዎች ጋር በማይቃረን መንገድ የአካባቢ ማህበራዊ ጉዳይ መመሪያዎችን አውጥቶ በቀበሌው ውስጥ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።
3. ከቀበሌው ምክር ቤት አባላት መካከል አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤና የቀበሌውን አስተዳደሪ ይመርጣል የቀበሌውን መስተዳድር ምክር ቤትም ያደራጃል።
4. በቀበሌው አስተዳዳሪ የሚቀርቡለትን የቀበሌውን ምክትል አስተዳዳሪና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ያፀድቃል።
5. የበላዩ በሆኑ የአስተዳደር አካላት የሚሰጡትን የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ልማት እና አስተዳደራዊ እቅዶችንና ፕሮግራሞችን መሠረት በማድረግ የስራ እፈፃፀም መርሀ ግብር ያወጣል አፈፃፀሙንም ይከታተላል።
6. የቀበሌውን የመስተዳድር ምክር ቤትና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን የስራ ክፍፍልና ምደባ ይወስናል።
7. ለቀበሌው ሕዝብ የሚጠቅሙ ሌሎች ተጨማሪ እቅዶችን ያወጣል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።
8. የቀበሌውን ሕዝብ ለልማት ስራ ያንቀሳቅሳል የተፈጥሮ ሀብትን ልማት እና እንክብካቤ ሥራ ይከታተላል።
9. በቀበሌው ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል።

## አንቀፅ 91
## ስለ ቀበሌ ምክር ቤት አመራር

1. የቀበሌ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል በሚመረጡ አንድ አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል።
2. አፈ ጉባኤው ምክር ቤቱን ይሰበስባል ይመራል አጀንዳዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ቃለ ጉባኤ መያዛቸውንና ሰነዶች መጠበቃቸውን ይቆጣጠራል።
3. ምክትል አፈ ጉባኤው በአፈ ጉባኤው ተለይቶ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል አፈ ጉባኤው በማይገኝበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሠራል።

## አንቀፅ 92
## የቀበሌ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የስራ ዘመን

1. የቀበሌ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከሁለት ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤት አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።

3. የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የስራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የስራ ዘመን በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲስ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።
4. የቀበሌው ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀፅ 93
## የቀበሌ የመስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀር

1. የቀበሌ የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት የቀበሌው አስተዳደሪ ምክትል አስተዳዳሪና በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙ የማህበራዊ አገልግሎት ሥጭ የመንግስት ተቋማት ሠራተኞች በአባልነት የሚገኙበት የበታች አስፈፃሚ አካል ነው።
2. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለቀበሌው ምክር ቤት።
3. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት በግልና በወል የቀበሌውን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ ያስተባብራሉ።
4. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በጋራ ስልጣናቸው ለሚያገለግሉት ውሣኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀፅ 94
## የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል
   ሀ. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት የልማት እቅዶችንና ፕሮግራሞችን ያወጣል ለቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
   ለ. የገጠር ልማትን ያፋጥናል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንክብካቤና ልማት ስራ እንዲካሄድ ያደርጋል ሕዝቡንም ለልማት ስራ ያነሣሣል ያስተባብራል።
   ሐ. የቀበሌው ሠላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል።
   መ. የስራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል።
   ሠ. በቀበሌው ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
2. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ዝርዝር የሥራ እቅዶችን የሚነድፈውና አፈፃፀማቸውን የሚከታተለውም ሆነ የሚገመግመው እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተገናኘ ይሆናል።

## አንቀፅ 95
## ስለቀበሌው አስተዳደሪ አሰያየምና የስራ ዘመን

1. የቀበሌው አስተዳዳሪ ከቀበሌው ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል።
2. በዚህ ሕገ መንግስት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ አስተዳዳሪው የስራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን ነው።

## አንቀፅ 96
## የቀበሌ አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌው አስተዳደሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና እንደ ሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት የወረዳ ወይም ከተማ መስተዳደር ሆኖ የቀበሌው ሊቀመንበር መስተዳደሩ ስራ መሪ የቀበሌ የመስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል
   ሀ. የቀበሌውን የመስተዳድር ምክር ቤት ይሰበስባል ይመራል።
   ለ. የበላይ በሆኑት የአስተዳደር አካላት የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና እቅዶች ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
   ሐ. የቀበሌውን ምክትል አስተዳዳሪ እና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ለቀበሌ ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል።
   መ. በቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት በቀበሌው ምክር ቤት እና እንደ ሁኔታው በሚመለከተው ከተማ ወይም ወረዳ መስተዳድር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀፅ 97
## የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ በቀበሌ አስተዳዳሪ ተመርጦ ተሹሞ በቀበሌው ምክርቤት የሚፀድቅ ሆኖ

1. በቀበሌው አስተዳዳሪና በመስተዳድሩ ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. የቀበሌው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይመራል።
3. የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለመስተዳድሩ ምክር ቤት ነው።

## አንቀፅ 98
## ስለ ቀበሌ መስተዳደር ጽሕፈት ቤት

1. የቀበሌ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት የመስተዳደር ምክር ቤት ጭምር ሆኖ ያገለግላል።
2. የቀበሌ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት እስከሚኖረው የቀበሌ አስተዳደሩን ጽሕፈት ቤትና የቢሮ መገልገያዎች በመጋራት ይሠራል።

## አንቀፅ 99
## የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የቀበሌው ማህበራዊ ፍርድ ቤት በዚህ ሕገ መንግስት የቀበሌው ማህበራዊ የዳኝነት አካል ሆኖ ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 4 ስር በተደነገገው መሠረት ተመርጠው የሚሾሙ ይሆናሉ።
3. የማህበራዊ ፍርድ ቤት የስራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን ነው።

# ምዕራፍ አስር
## የክልሉ ፖሊሲ አላማዎች

## አንቀፅ 100
## አላማዎች

1. ማንኛውም የመንግስት አካል የፌዴራሉንና የክልሉን ህገ መንግስት ሌሎች ህጎችና ፖሊሲዎችን በስራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት አላማዎች እና መርሆዎች ላይ መመስረት አለበት።
2. በዚህ ምዕራፍ "መንግስት" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ይሆናል

## አንቀፅ 101
## ፖለቲካ ነክ አላማዎች

1. መንግስት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት የአፋር ክልል ህዝብ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።
2. መንግስት የብሔረሰቦችና የህዝቦች ማንነት የማክበር በዚህ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸዉ እኩልነትን አንድነትን ወንድማማችነትን የሚጠናከር ግዴታ አለበት።

## አንቀፅ 102

## ኢኮኖሚ ነክ አላማዎች

1. መንግስት ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ በተጠራቀመ ዕዉቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ሀላፊነት አለበት።
2. የክልሉ ኢኮኖሚ በዋናነት የተመሠረተው በእንስሳት ሀብት በመሆኑ መንግሥት ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ሲቀርፅ የአርብቶ አደሩን የኑሮ መሠረት በማሻሻል ወደ ተረጋጋ ኑሮ የሚመጣበትንና የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሃላፊነት አለበት።
3. መንግስት የክልሉ ነዋሪዎችን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል ዕኩል እድገት እንዲኖራቸዉ ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት።
4. መንግስት የተፈጥሮና የሠው ሠራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋዉ ሲደርስም ለተጐጂዉ እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።
5. መንግስት የክልሉን ኢኮኖሚ ከሀገር አቀፍ ኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ከፌዴራል መንግስት አካላት ጋር ጥረት ያደርጋል።
6. መንግስት የግል ባለሀብቶችን በክልሉ ልማት እንዲሳተፍ ያበረታታል፤ አስፈላጊውንም እገዛ ያደርጋል።
7. መንግስት መሬትንና ተፈጥሮ ሀብትን በህዝብ ስም በይዞታዉ ስር በማድረግ ለህዝቡ የጋራ ጥቅምና ዕድገት እንዲዉል የማድረግ ሀላፊነት አለበት።
8. መንግስት የክልሉ የልማት ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት ህዝቡን በየደረጃዉ ማሣተፍ አለበት የህዝቡንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት።
9. መንግስት የህዝቡን ዕዉቀት ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት። ህዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረዉ ማድረግ አለበት ስለሆነም ህዝቡ ዕቅዶችና ፖሊሲዎችን ለመደገፍ ብቻ ሳይሆን በማስፈፀምና በመገምገም መሳተፍ አለበት።
10. መንግስት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።
11. መንግስት የሠራተኛዉን ህዝብ ጤንነት ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት።

## አንቀፅ 103
## ማህበራዊ አላማዎች

1. የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህርት የጤና አገልግሎት የንፁህ ውሃ የመኖሪያ የምግብና ማህበራዊ ዋስትና እንዲያገኙ ያደርጋል።
2. ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶች፣ ከባህላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ ይካሄዳል።

## አንቀፅ 104
## ባህል ነክ አላማዎች

1. የክልሉ መንግስት መሠረታዊ መብቶችንና ሠብአዊ ክብርን ዲሞክራሲንና ህገ መንግስቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የያንጉዲራሳና የአዋሽ ፓርኮችን የፌዴራሉ መንግስት ከሚያደርገው ጥበቃ በተጨማሪ የክልሉ መንግስትና ህዝብ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው።
3. የክልሉ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት።
4. መንግስት ወጣቱን ትውልድ የመንከባከብ በተሟላ ሥነ ምግባር የማነፅ፣ ከሱስ ነፃ የሆነና፣ በአካልም ሆነ በአዕምሮ ጠንካራ ኃላፊነትን የሚሸከም፣ አገሩን የሚወድ እና ለወገኑ የሚቆረቆር ብቁና በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
5. የክልሉ የሥራ ቋንቋ ስለሆነው የአፋርኛ ቋንቋ ዕድገት መንግስት ልዩ ትኩረት በመስጠት ይንቀሳቀሳል።
6. የክልሉ መንግስትና ህዝብ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የአርኪኦሎጂ ግኝቶችና የታሪክ ቅርሶችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀፅ 105
## የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ አላማዎች

1. መንግስት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት።
2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።
3. የህዝብን የአካባቢ ደህንነት በሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ህዝብ ሀሳቡን እንዲገልፅ ማድረግ አለበት።

4. መንግስትና የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው። በተለይ በረሃማነትን ለመከላከልና ለመግታት መንግስትና ህዝብ አስፈላጊውን ሁሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

# ምዕራፍ አስራ አንድ
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀፅ 106
## የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1. በፌደራሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 93 ንዑስ አንቀፅ አንድ(1) (ሀ) እና (ለ) እና በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ(47) አርባሰባት ንዑስ አንቀፅ(2) ሁለት(ጠ) በተደነገገው መሠረት ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ባልሆነበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ ሀምሳ ስምንት (58) ንኡስ አንቀፅ (7) በተሠጠዉ ስልጣን መሠረት ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አዉጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል።
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌዉን አዉጥቶ በስራ ላይ ባዋለ በአስራ አምስት ቀን ዉስጥ አፈ ጉባኤዉ የክልሉን ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማሳወቅና የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉን ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማፀደቅ አለበት።
3. የክልሉ መስተዳድር ያወጣዉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በክልሉ ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለዉ ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉን በየአራት ወሩ እንዲታደስ ለማድረግ ይችላል። ይህን በስራ ላይ ማዋል የሚችለዉ ግን ለሶስት ጊዜ ብቻ ነዉ።
4. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸዉ ደንቦችና የሚወስዳቸዉን እርምጃዎች በማናቸዉም ረገድ በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ 15 አንቀፅ 16 አንቀፅ 18 (1) እና (2) ፣ 21 (1) ፣ 24 (1) ፣ 27 (1) እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸዉም።

## አንቀፅ 107
## የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

1. የክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸዉ ሰባት የቦርዱ አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ መርማሪ ቦርድ ማቋቋም ይችላል። ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌዉ በክልል ምክር ቤት በሚፀድቅበት ጊዜ ይቋቋማል።
2. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ሀላፊነቶች ይኖሩታል።
   ሀ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሠሩትን ግለሰቦች በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ይፋ ማድረግና የተሠሩበትን ምክንያት መግለፅ።
   ለ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ወቅት የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸዉም ረገድ ኢሰብአዊ አለመሆናቸዉን መቆጣጠርና መከታተል
   ሐ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እርምጃዎች ኢሰብአዊ ድርጊት የፈፀሙትን ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ
   መ. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እንዲቀጥል ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለዉን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ ።

## አንቀፅ 108
## የክልሉ ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማል።
2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉ መንግስት ተቋማትና የሌሎች መስሪያ ቤቶችን ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልል ምክር ቤት የተመደበዉ አመታዊ በጀት በበጀት አመቱ ዉስጥ እንዲሠሩ ለተወሠኑት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።
3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመስሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል
4. የዋና ኦዲተር ተጠሪነት ለክልል ምክር ቤት ይሆናል።
5. የዋና ኦዲተር ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 109
## የህገ መንግስት ማሻሻያ ሀሳብ ስለማመንጨት

የዚህ ህገ መንግስት ማሻሻያ ሀሳብ አጀንዳ ሆኖ ለዉይይት የሚቀርበዉ

ሀ. በክልሉ ምክር ቤት አባላት አንድ ሶስተኛ ጥያቄ ወይም

ለ. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአብላጫ ድምፅ ዉሳኔ ወይም

ሐ. በክልሉ ዉስጥ ካሉ የወረዳ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛዉ ተቃዉሞ ወይም

መ. በክልሉ ዉስጥ ካሉ የቀበሌ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛዉ የተጠየቀ ከሆነ ለዉይይትና ለዉሳኔ የህገ መንግስቱ መሻሻል ለሚመለከታቸዉ ክፍሎች ይቀርባል።

## እንቀፅ 110
## የህገመንግስት ማሻሻል

1. የዚህ ህገ መንግስት ምዕራፍ ሁለትና ሶስት የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚሻሻሉት በፌደራል ህገ መንግስት አንቀፅ 105 መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ከተዘረዘሩት ዉጭ ያሉት የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለዉ አካኋን ብቻ ይሆናል፡፡
   ሀ. በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአብላጫ ድምፅ ሲያፀድቁት፣
   ለ. በክልሉ ምክር ቤት አባላት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀድቁት ነዉ፡፡
3. የዚህ ንዑስ አንቀፅና የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ሁለት ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የቀረበዉን ማሻሻያ፣
   ሀ. በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙ ወረዳ ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ብልጫ ሲያፀድቁትና፣
   ለ. የክልሉ ምክር ቤት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀድቁት ነዉ፡፡

## እንቀፅ 111
## የመጨረሻ ህጋዊ ኮፒ

የዚህ ህገ መንግስት የአፋርኛ ቅጅ የመጨረሻዉ ህጋዊ ዕዉቅና ያለዉ ሆኖ ነዉ።